**ሞንትጎመሪ ካውንቲ የመጓጓዣ ዲፓርትመንት**

**አጠቃላይ የአውቶቡስ ኔትወርክ ጥናት**

**"ራይድ ኦን እንደገና በምናብ"**

**መግቢያ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ራይድ ኦን የአውቶቡስ አገልግሎት ከ 40 አመታት በላይ ስራ ላይ ቆይቶዋል፤ ይህም በካውንቲው ለሚኖሩ እና ለሚሰሩ ሰዎች ወሳኝ የመንቀሳቀሻ አማራጭ በመሆን ነው። ከጊዜ በሁዋላ፣ የራይድ ኦን የስብጥሩን እና የመሬት አጠቃቀሙን ለውጥ ላይ በመመርኮዝ የመስመር አደረጃጀቶቹ አድገዋል። ካውንቲው በህዝብ ብዛት፣ ስብጥር፣ የቅጥር ማእከላት፣ እና መኖሪያ ቤቶች ላይ የሚታዩትን ለውጦች በመከተል፣ የስርአቱን አጠቃላይ ግምገማ የማድረጊያው ጊዜ አሁን ሲሆን፣ በተለይ ደግሞ ከኮቪድ-19 ስርጭት ጋር የሚጠበቁ ለውጦች እንደተጠበቁ ሆነው ማለት ነው።

የራይድ ኦን እንደገና በምናብ አጠቃላይ የወደፊት የአውቶብስ ስርጭት ምዘና ሲሆን፣ ይህም በወደፊት እና በአሁን ፍላጎቶች ላይ ተመስርቶ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ስምሪቱ ላይ ጉልህ የሚፈለጉ ለውጦችን ሊፈጥር ይችላል። ይህ ጥናት የሞንትጎመሪ ካውንቲ አጠቃላይ ያለውን እና የታቀደውን መጓጓዣ ስርአት በጥልቀት የሚመረምር ሲሆን፣ ይህም በካውንቲው ክልል ውስጥ የሚሰሩ የሜትሮባስ አገልግሎቶችን እና የወደፊቱ ፐርፐል ላይንን ጨምሮ ይሆናል። ጥናቱ በተጨማሪም መረጃ ትንተና እና ማህበረሰባዊ ተሳትፎ በመጠቀም የራይድ ኦንን ወደፊት ለመምራት እድል ይሰጣል። ጥናቱ ተቀዳሚ አላማው ስርአት አቀፍ ለውጦችን በማቅረብ ለራይድ ኦን እና ሜትሮባስ አገልግሎቶች ለሚጠቀሙ ማህበረቦች ያለውን የአሁን እና የወደፊት ፍላጎቶች ለማዳረስ ይጠቅማል።

ጥናቱ የራይድ ኦን አገልግሎት ቦታዎች የአሁን ሁኔታዎች እና የሚጠበቁ የወደፊቶችን ሲመረምር፣ የሚያሳትፈውም የማህበረሰብ መሪዎችን፣ አንቂዎችን፣ የትራንዚት ተሳፋሪዎችን እና የድጋፍ ድርጅቶችን ሲሆን ይህም የመጓጓዣ አማራጭ መሰረቶችን ለመፍጠር ይሆናል። ሙሉ ግምገማ በማድረግ የጉዞ መዋቅር፣ መገናኛ፣ ስፋት፣ እና የአገልግሎት ፍጥነትን በገበያ ጥናት እና ትንተና፣ በመሬት አጠቃቀም ማጎልበት እና በሚጠበቁ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች በግምገማው ይዳሰሳሉ። ጥናቱ በተጨማሪም የካውንቲው ቅድሚያዎችን የዘር እኩልነትን ለማሻሻል እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ይዳሰሳል። የትራንዚት አገልግሎቶች ምስል ተጓዦችን ለመሳብ አስፈላጊ ነው፤ ስለዚህ፣ የራይድ ኦን የውስጥ እና የውጭ ግምገማ ይፈተሻል። በማጠቃለያው፣ ጥናቱ የሚፈጥረው የእቅድ አቅጣጫን እንዲሁም ከአጠቃላይ የመጓጓዣ ስርጭት አላማዎቻችን ጋር የበለጠ የሚያስማሙ ምክረ ሃሳቦች እና የመተግበሪያ ስትራቴጂዎችን ነው።

ለአሁን እና ለወደፊት የአውቶቡስ ተሳፋሪዎች አገልግሎቶችን ለማሻሻል እና ለማሳደግ ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ ናቸው። እቅዱ የአገልግሎት ጥራትን በጉዞ ደረጃ እና አገልግሎት አይነቶች የሚገመግሙ ደረጃዎችን እና አላማዎችን ያቀርባል።

**የአሁን ሁኔታዎች**

ጥናቱ የሚያካትተው የራይድ ኦን የአሁን እና የቅድመ ኮቪድ ሁኔታዎችን ነው። የሚከተሉት ስራዎች የአሁን ሁኔታዎች ዝርዝር መግለጫዎችን ያሳያሉ፥

1. በካውንቲው ክልሎች ውስጥ እንዲሁም እንደ ፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ እና ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በመሳሰሉ የዙሪያ ቦታዎች ላይ የአገልግሎት ቦታ እና የመስመር ግንኙነቶችን ይገመግማል።
2. የአሁን አገልግሎቶችን የተሳፋሪ መረጃን ከኤቪኤል ኤፒሲ መረጃ፣ ዳሰሳ መረጃ፣ ብቃት መረጃ እና ሌሎች ከአገልግሎት ብቃቶች ጋር የተዛመዱ ዳታቤዞችን መሰብሰብ።
3. የተሳፋሪ መጠቀሚያ ነገሮችን መገምገም ይህም የአውቶቡስ መቆሚያ፣ የአውቶቡስ መጠለያ፣ የጉልበት ግድግዳዎች፣ የአውቶቡስ ጣቢያ ስፍራዎችን፣ አቁሞ መሳፈሪያ ቦታዎችን እና የአውቶቡስ አሽከርካሪ መጸዳጃ ቤቶችን ያጠቃልላል።
4. የሪልታይም (የጉዞ ማቀጃ)፣ ካድ ኤቪኤል እና ፌርቦክሶችን መገምገም። ሁኔታውን፣ አጠቃቀሙን፣ እና የአገልግሎቶች ተደራሽነታቸውን መግለጽ።
5. የመነሻ መድረሻ ተለምዶዎችን መገምገም የመጀመሪያ የመጨረሻ ግንኙነቶችን ጨምሮ።
6. አጠቃላይ ብቃት መገምገም ይህም የሚከተሉትን የአገልግሎት ደረጃዎች እና ከምርጥ የኢንዱስትሪ ልምዶች ማነጻጸሪያዎችን የሚከተል ማትሪክስ በመጠቀም ይህም ከአገልግሎት ስፋት እና ደረጃዎች ጋር የሚጣጣሙ የተቋቋሙ የፒር ቡድኖች ጋር የሚሄድ።
    a. ብዛት

b. የአገልግሎት ፖሊሲ ስፋት ይህም የሙሉ ቀን፣ የፒክ ጊዜያት፣ እና የምሽት ጊዜያት የሚያገለግሉ መስመሮችን ጨምሮ።
c. የመስመር ክፍፍል ይህም የተወሰኑ መስመሮች፣ የተገደቡ መቆሚያዎች፣ የፈጣን አገልግሎቶች፣ እና የጥሪ አገልግሎቶችን ይጨምራል።
d. የአሁን የክፍያ መዋቅር እና የወደፊት የተወጠኑ የክፍያ መዋቅሮች
e. የበጊዜ መገኘት ብቃት
f. የታለፉ ጉዞዎች
g. የሞሉ አውቶቡሶች
h. የተጓዥ ቅሬታዎች
i. የተሽከርካሪው የመጫን አቅም

7. በካውንቲ ወሰኖች ውስጥ ያለውን የአገልግሎት ሽፋን መገምገም። ይህም የአካባቢውን እና የክልሉን አገልግሎቶች በመላ የትኛውንም አቅራቢ ላይ ሳይወሰን የመገምገም እድል ሲሆን፤ በተለይ የራይድ ኦን እና ደብሊውኤምኤቲኤ ደግሞ። የነዚህን አገልግሎቶች የሚመለከቱ አላማዎች እና ምደባዎችን ይግለጹ።

a. ራይድ ኦን ፡ የአካባቢ አገልግሎት
b. ኤክስትራ ፡ የውስን ማቆሚያ አገልግሎት
c. ፍላሽ ፡ ቢአርቲ
d. ፍሌክስ ፡ የበጥሪ አገልግሎት
e. ደብሊውኤምኤቲኤ ፡ ሜትሮባስ
f. ኤምቲኤ ኮሙተር አውቶቡስ አገልግሎት
g. ሽትል ዩኤም
h. ቤተስዳ ሰርኩሌተር
i. ደብሊውኤምኤቲኤ ሜትሮሬይል (ሽፋን)
j. ፐርፐል መስመር

## ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች

የአገልግሎት ደረጃዎች የስኬታማ ውጤት የጀርባ አጥንት ናቸው። የተሻሻሉ ፖሊሲዎች እና ደረጃዎች መቋቋም ለወደፊት የበጀት እና እቅድ ውሳኔዎች የአገልግሎቶች መገምገምን መሰረት ይጥላል።

1. ስርአቱ እንዴት እንደሚዋቀር ለመምራት የአገልግሎቶች መመሪያዎችን ማየት፣ መፍጠር እና መደንገግ። አዳዲስ መመሪያዎች መፈጠር ይችላሉ፣ ወይም ደግሞ የተሻሻሉ የአገልግሎት ዝርዝሮች በደብሊውኤምኤቲኤ ከክልሉ አስተያየት ጋር ተደምሮ መሰራት ይችላል።
   a. ከፍተኛ ቁጥር
   b. ፍጥነት
   c. ሽፋን
   d. ማይክሮትራንዚት

2. ለሄድወይስ እና የአገልግሎት ስፋት መመሪያዎችን መፍጠር፤ የበፊት ሄድወይ ደረጃዎች በማንኛውም መስመር ከ 30 ደቂቃዎች አይበልጡም ነበር። ይህ ፖሊሲ አሁንም በዚህ አዲስ ሁኔታ (ድህረ ኮቪድ) እንደሚሰራ ማየት።

3 . የስርአቱን የአገልግሎት ስፋት በየመስመሩ መገምገም። ለአገልግሎት ስፋት የድርጊት ፓሊሲን በየመስመሩ መዋቅር ወይም ቅርጽ መደንገግ።

4. ለክፍያ ፖሊሲዎች ቅርጾችን ለወደፊቱ ማስቀመጥ። የበሽታ ስርጭት ማገገምን የሚዳስሱ አራት ቢሆኖችን የሚገመግም የተለየ ጥናት እየተካሄደ ነው፥

a. ዜሮ ክፍያ ስርአት በሰፊው
b. ዜሮ ክፍያ በተወሰነ የቀኑ ጊዜያት

c. ቅናሽ ክፍያ ($1)
d. ነጻ ወይም ቅናሽ ክፍያ ለዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ህዝቦች (ገቢን መሰረት ያደረገ ሃሳብ)

**የአውቶቡስ ስርጭት ምዘና**

ከጊዜ በሁዋላ፣ በጥያቄ፣ በስነ ህዝብ ፍላጎቶች፣ እና በመልሶ መጎልበት የተነሳ የተፈጠሩ የአገልግሎት መስፋፋቶች እና አዳዲስ የመስመር ቅርጾች አሉ። የጥናቱ ጉልህ ክፍል የሚያተኩረው አገልግሎቱን በተለያዩ እይታዎች በድጋሚ በምናብ ማየት ላይ ነው። እነዚህ ዋና የትኩረት ቦታዎች የሚጨምሩት፥

<u>የገበያ ትንተና</u>

1. ለራይድ ኦን እና ሜትሮባስ አገልግሎቶች የመነሻ እና መድረሻ (ኦ ዲ) የጉዞ ምህዳሮች ትንተና
2. ያለውን የትራንዚት አጠቃቀም የሚረዳ የ ትራንዚት ፕሮስፐንሲቲ ኢንዴክስ (ቲፒአይ) መለየት
3. በአገልግሎት ቦታ ውስጥ ያለውን ትራፊክ ትንተና ዞን (ቲኤዝ) ማየት
4. ያለው መዋቅር እያደገ እና እየተስፋፋ ያለውን ማህበረሰባችን ፍላጎት እንደሚያረካ የሚመረምር የአጠቃላይ የስርአት ቅርጽ መገምገም
5. ያሁንን መዋቅር መገምገም እና እንዴት የተለያዩ አገልግሎቶች ከአውቶቡስ ፈጣን ትራንዚት (ቢአርቲ) ጋር እንደሚቀናጅ መገምገም
    a. ለአካባቢው አውቶቡስ አገልግሎት (ራይድ ኦን እና ሜትሮባስ) እና ቢአርቲ አገልግሎቶች የስርአት ቅርጽ መፍጠር።
6. ያለፉት የተሰናዱ ዳሰሳዎችን ማየት።
7. ያካባቢው ኮሌጆች፣ ትምህርት ቤቶች፣ መዝናኛ ማእከላት፣ መጽሃፍት ቤቶች፣ እና በአገልግሎት ቦታ ያሉ ዋና መናፈሻዎችን መገምገም።

**የመሬት አጠቃቀም መጎልበት መጓጓዣ እቅዶች**

የተለያዩ ጥናቶች ባለፉት ብዙ አመታት ተደርገዋል። ያለፉት ጥናቶችን ገምግሞ የራይድ ኦን እንደገና በምናብ ማየት ከአጠቃላይ የካውንቲው እቅዶች ጋር የተጣመረ መሆኑን ማየት አስፈላጊ ይሆናል። የሚከተሉት እቅዶች በግምገማው ውስጥ መካተት ይኖርባቸዋል፥

1. ቤተስዳ ትራንዚትወይ
2. አውቶቡስ ስምሪት መምሪያ እቅድ
3. አውቶቡስ ፈጣን ትራንዚት ኮሪደሮች
4. አውቶቡስ መበልጸጊያ ጥናት
5. ሲሲቲ
6. ሆት ሌንስ/I-270 የተመሩ ሌኖች
7. ፐርፕል መስመር
8. የጋራ መስመሮች የብስክሌት መንገዶች
    a. የጋራ መንገዶች ፕሮግራሙን ማየት እና መገምገም። ለተንሳፋፊ የአውቶቡስ መቆሚያዎች እና የእግረኛ መሻገሪያ ፕሮቶኮሎችን መረዳት።
    b. ለአውቶቡስ የቅድሚያ ሌኖች በሙከራ ላይ ያሉ ስፍራዎችን መገምገም እና ተጨማሪ ቦታዎችን እንደ ቲኤስፒ፣ ተራ ዝለላዎች፣ ወዘተ ያሉትን ምክረ ሃሳብ ማቅረብ፣ እንዲሁም በአውቶቡስ ስርጭቱ ላይ ያላቸውን ተጽእኖ መረዳት

c. የአውቶቡስ ሌኖች በጥራት እና በአስተማማኝነት ላይ አጠቃላይ ስርአቱን ለማሻሻል ትልቅ ተጽእኖ የት እንደሚኖራቸው መመርመር።

9. ትራይቭ 2050

10. ሞንትጎመሪ ካውንቲ የአየር ንብረት የተግባር እቅድ

11. ራእይ ዜሮ

12. ታላቁ የሴኔካ ሳይንስ ኮሪዶር (ጂኤስኤስሲ)

13. የእይታ ስንኩልና ላለባቸው ሰዎች መንገዶችን ደህንነታቸው የተጠበቀ እና የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ መገዶችን ማቀድ እና መቅረጽ

14. ማስተር እቅዶች

   a. የአካባቢ ማስተር እቅዶች
   b. የሴክተር እቅዶች
   c. ስራ ላይ የሚውሉ ማስተር እቅዶች

15. ኮሪዶር የወደፊት

16. ለተለያዩ የትራንዚት ማእከላት የህንጻ እቅድ ጥናቶች

__መሰረተ ልማት__

ማረፊያ ቦታዎች አዳዲስ ተሳፋሪዎችን ለመሳብ እና የአሁን ተሳፋሪዎችን ይዞ ለመቆየት ፈጠራ በተሞሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እና ኢንቨስትመንቶችን የማቅረብ እድል ያቀርባሉ። የነዚህን ፕሮግራሞች ተግባራዊነት መረዳት አስፈላጊ ነው።

1. የአሁን የአውቶቡስ ማቆሚያ ጋራዦችን መገምገም እና እቅዱን የበለጠ ለመደገፍ የመስፋፊያ ስትራቴጂዎች ምክረ ሃሳብ መስጠት።
2. የተሳፋሪ ማረፊያ ሙሉ ፕሮግራሞችን መገምገም ይህም የአውቶቡስ ማቆሚያ እና የአውቶቡስ መጠለያ ፕሮግራምን ይጨምራል።
3. የአውቶቡስ መቆሚያ መለያን ኮዶችን እና ስምሪቶችን በተለያዩ አገልግሎቶች የምዘና ሂደት ውስጥ መረዳት እና ማወቅ።
4. በአውቶቡስ መቆሚያ ምልክቶች እና የአውቶቡስ መጠለያዎች ላይ ያለውን መረጃ እንዲሁም የወዲያውኑ ጊዜ ድርጊቶችን መገምገም እና መረዳት።
5. የአውቶቡስ መቆሚያ፣ የአውቶቡስ መጠለያዎች፣ የአውቶቡስ ጣቢያዎች፣ የጉልበት ግድግዳዎች እና የአውቶቡስ አሽከርካሪ መጸዳጃ ቤቶች ጥገናን መገምገም።
6. የአቁሞ መንዳት ስፍራዎች የአሁን ስምሪቶችን መገምገም።
7. የትራንዚት ማእከሎች እና ለቢአርቲ አገልግሎቶች የተገነቡ የትራንዚት ጣቢያዎችን የአሁን ክንውኖች መረዳት።
8. የነዚህን ትራንዚት ማእከሎች ለመግለጽ በአሁኑ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋሉ የተለያዩ መገለጫዎችን ያካቱ። እነዚህ ስፍራዎች ከሜትሮ ጣቢያዎች ጋር ያልተዛመዱ እና ቢያንስ ሶስት ወይም ከዛ በላይ መስመሮች ለመተላለፊያ የሚያገለግሉ ናቸው።
   a. ጀርመንታውን ትራንዚት ማእከል

b. ሌክፎረስት ትራንዚት ማእከል
c. ማይልስቶን ትራንዚት ማእከል
d. ትራቪል ትራንዚት ማእከል
e. ወስትፊልድ ሞንትጎመሪ ሞል
f. ቦይድስ ትራንዚት ማእከል
g. ዋይት ኦክ ትራንዚት ማእከል

9. ለአውቶቡስ ማቆሚያ ማስፈሪያ እንዲሁም የጎን መራመጃ መግቢያ እና መሻገሪያ መመሪያዎችን መገምገም እና ማጎልበት

10. የአውቶቡስ መቆሚያ ስፍራዎችን ከወይፋይንዲንግ ጋር ለመርዳት ያለውን ማስረዳት መገምገም እና ምክረ ሃሳብ ማቅረብ።

11. የአውቶቡስ ስፍራዎችን ከሞኒተር የዓሁን ጊዜ መረጃ ያላቸው መገምገም እናም ያሉትን መረጃዎች እና አፖች በማጠቃለያነት የሚጠቀም ምክረ ሃሳብ ማቅረብ።

a. አውቶቡስ ማቆሚያ መጠለያ ቆጠራ ጥናት
b. አውቶቡስ ማቆሚያ ዳታቤዝ

**ቴክኖሎጂ**

በኤምሲዲኦቲ ትራንዚት መምሪያ ውስጥ ያሉ ብዙ የቴክኖሎጂ መነሳሳቶች አሉ፤ እናም የተለያዩ ፕሮጄክቶች እና አሰራራቸውን መረዳት አስፈላጊ ይሆናል። ያረጁ ሲስተሞችን ማሻሻል፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የዘር እኩልነት እና የደንበኛ መረጃ ለካውንቲው የሚጠቀሱ አንዳንድ ተቀዳሚዎች ናቸው።

1. አዲሱን ሲኤድ ኤቪኤል ስርኣት (ክሌቨር መሳሪያ) መረዳት ማምጣት እና በስርኣቱ ውስጥ ያለውን አሰራር መገምገም።

a. ኤፒሲ መረጃ
b. ራይድቼክ ፕላስ

2. ወደ ዜሮ ልቀት አውቶቡሶች ለምሳሌ ኤሌክትሪክ፣ ባትሪ ኤሌክትሪክ አውቶቡሶች እና ሃይድሮጅን ፊውል ሴል አውቶብሶች፣ ለመሻገር እቅድ ምክረ ሃሳብ ማቅረብ።

3. መስመሮችን ከኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ አቅሞች እና መሰረተ ልማቶች ጋር የበለጠ የማስማማት እቅድ እንዲሁም በስራ ላይ እያለ ለቻርጅ ማረጊያ ጣቢያዎች ጋር የሚናገር ቴክኖሎጂ እቅድ ማጎልበት።

4. ወደ ዜሮ ልቀት አውቶብሶች የሚቀየሩበትን የጊዜ ሰሌዳ መገምገም እና የኤሌክትሪክ መስመሮች መመሪያን ማቅርብ።

5. በቢአርቲ ጣቢያዎች ላይ የከቦርድ ውጪ የክፍያ መሰብሰብን መገምገም እና ለስርጭቱ ያለውን ውጤታማነት እና ጥቅም መተንተን።

6. የአሁን ጊዜ መረጃ ሁኔታን መገምገም።

7. ለአሁን ጊዜ መረጃ ስራ ላይ መዋል እና ለተጠቃሚዎቹ ያለውን ተደራሽነት መገምገም።

8. የተሽከርካሪ ኦቶሜሽን መዳሰስ።

9. የበጥሪ አገልግሎቶች ለምሳሌ ፍሌክስ ወይም አሊስ፣ መስፋፋታቸውን መገምገም።

<u>**ስራዎች / ስምሪት**</u>

እቅድን ለመተግበር ወሳኙ ክፍል አገልግሎቱ እንዴት እንደሚቀርብ ነው። የስራ መዋቅሩን መረዳት አስፈላጊ ይሆናል።

1. የዴፖ መዋቅር፣ የስራ ውጤታማነት እና የእድገት አቅጣጫዎችን በተለይ ወደ ዜሮ ልቀት አውቶብሶች ያሉትን መገምገም እና ምክረ ሃሳብ ማቅረብ።
2. ደረጃ ያላቸው የስራ መመሪያዎችን መገምገም እና በኢንዱስትሪው ካሉ ምርጦች ጋር ማነጻጸር።
3. የስምሪት አይነቶችን እና የአገልግሎት ስፍራዎችን ለዘር እኩልነት መገምገም።
4. የስራ ውቅሩን ውጤታማነት መገምገም እና በኢንዱስትሪው ካሉ ምርጦች ጋር ማነጻጸር።
5. የራይድ እና የደህንነት እና የስልጠና ፕሮግራምን ለመገምገም እቅዶች አሉ። ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ሂደቱን መረዳት እና እቅዶቹን ማየት አስፈላጊ ይሆናል። የሂደቱ ምዘና እና የኢንዱስትሪው ምርጦች የእቅዱ አካል መሆን አለበት።
6. የአውቶቡስ አሽከርካሪዎችን ለመሳብ እና ይዞ ለማቆየት የሚሆኑ አዳዲስ ስትራቴጂዎችን ምክረ ሃሳብ ማቅረብ፣ ይህንንም በጥናት እና የኢንዱስትሪውን ምርጦች እንደ መመሪያ በመጠቀም።

<u>**ገበያ ጥናት**</u>

ተጓዦችን እና ግንዛቤን ለመጨመር ሌላው ወሳኝ ነገር ግልጽ እና አጭር መልእክት መጠቀም ነው።

1. ያለውን የአሁን መረዳት መገምገም እና የሪብራንዲንግ አማራጮችን እና መመሪያዎችን ምክረ ሃሳብ ማቅረብ
2. በደንበኛ ርካታ ዳሰሳ በኩል የአሁን ተጠቃሚዎችን አስተያየት መገምገም።
3. የአሁን ምልክቶችን መገምገም እንዲሁም ለተጨማሪ ግንዛቤ ምክረ ሃሳብ ማቅረብ።
    a. ወይፋይንዲንግ ምልክት
    b. የውጭ ግንኙነት የአውቶቡስ መቆሚያ ምልክት ጨምሮ

4. ካርታዎችን እና የጊዜ ሰሌዳዎችን መገምገም እና ለወደፊት ጥራት ከእኩያ ቡድኖች ጋር በመሆን ምክረ ሃሳብ ማቅረብ።

5. የትራንዚት ዲቪዚዮን ድረገጽ በመገምገም ወሳኝ መረጃ ከብቃት መለኪያዎች፣ ክፍያዎች፣ መስመሮች፣ ሰሌዳዎች፣ ማህበረሰብ ሚዲያ፣ እና አጠቃላይ ግንኙነቶች መካተታቸውን ማየት።

6. ከመረጃ መዳረስ ጋር የተያያዘ የአሁን ልምዶችን መገምገም።

## ባለ ድርሻ አካላት

በዚህ ጥናት ላይ ራእይ መመስረት እና ከባለ ድርሻ አካላት አስተያየት መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ባለድርሻ አካላቱ በመነሻ ደረጃው ላይ የሚካተቱት መመሪያ እና መዋቅር ለማግኘት ነው። በፕሮጀክቱ የተለያዩ ደረጃዎች ላይ ቀጣይነት ያለው መሻሻሎች ይጠየቃሉ። ይህ ዝርዝር በሙሉ የሚያጠቃልል ስላልሆነ ሌሎች ሊጨመሩ ይችላሉ።

1. ስራ አስፈጻሚ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች
2. ካውንቲ ምክር ቤት
3. ሜሪላንድ ብሄራዊ ካፒታል መናፈሻ እና የእቅድ ኮሚሽን (ኤምኤንሲፒፒሲ)
4. የአካባቢ ክፍለ ከተማዎች
5. የአውቶቡስ አሽከርካሪዎች የሱቅ ሰራተኞች ኤምሲጂኢኦ

6. ደብሊውኤምኤቲኤ ሜትሮባስ
7. ትራንዚት ተሙዋጋች ቡድኖች
8. ሜትሮፖሊታን ዋሽንግተን የመንግስት ካውንስል (ኤምደብሊውሲኦጂ)
9. ሜሪላንድ የመጓጓዣ ዲፓርትመንት (ኤስኤችኤ ኤምቲኤ)
10. ኤምሲዲኦቲ የተመላላሽ አገልግሎቶች ቲዲኤም
11. ሞንትጎመሪ ካውንቲ የንግድ ስራ ምክር ቤት
12. ሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች
13. የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት መስሪያ ቤቶች
14. ኤችኦሲ እና ኤችኦኤ ማህበራት

**የህዝብ ተሳትፎ**

ለዚህ ጥናት ስኬት ግልጽነት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ክፍት ግንኙነት ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በሁልጊዜ ቀጣይነት እንዲሁም የህዝብ የተሳትፎ ሂደት እጅግ ወሳኝ ነው።

1. ለትብብራዊ ውይይት የሚተጋ የህዝብ ተሳትፎ እቅድ ማጎልበት።
2. ለግንኙነት መሰረታዊ መንገዶች፣ እንደ ፕሮጀክት ድረገጽ፣ ማህበረሰብ ሚዲያ፣ የድንገት ስብሰባዎች፣ በመጠቀም ደንበኞች በሚሳፈሩበት ቦታዎች መድረስ።
3. ከተለያዩ የትራንዚት ተሙዋጋች ቡድኖች፣ ሲቪክ ማህበራት፣ ማህበረሰብ ቡድኖች፣ ወዘተ ጋር ህዝባዊ ስብሰባዎችን ማድረግ።
4. በጥናቱ አጠቃላይ ሂደት ላይ የፕሮጀክቱ ቡድን ይሳተፋል። ስለዚህ፣ የተደነገጉ ውጤቶች በሂደቱ መጀመሪያ ላይ ይገለጻሉ።
5. በአፍ እና በጽሁፍ ቋንቋዎች በመደገፍ ለአገልግሎቶች ትርጉም ያለው ተደራሽነት የሚያቀርቡ የተደራሽነት መረጃዎችን ማጎልበት። ከአጠቃላይ ከሚገመገመው ህዝብ 5% ወይም 1000 ሰዎች፣ ያነሰው፣ ለሚኖሩ ሁሉም ቋንቋዎች ትርጉም ሊቀርብ ይገባል። የነዚህ መሳሪያዎች ምሳሌዎች የሚያጠቃልሉት፥
    a. ካርታዎች
    b. የሚዲያ ማስታወቂያዎች
    c. ማሳሰቢያዎች ለስርጭት
    d. ፕሮጀክት ድረገጽ
    e. የስብሰባ አጀንዳዎች
    f. ፓወርፖይንት ገለጻዎች
    g. ዲስፕሌይ ቦርዶች
    h. ቪዡዋል ደጋፊዎች ለተለያዩ ተደራሾች የሚቀርቡ እና ግልጽ የሆኑ

5. ለሁሉም ግንኙነቶች እና ቆጠራዎች የስብሰባ ጽሁፎችን ማቅረብ።

**የአገልግሎት ሃሳቦች እና ምክረ ሃሳቦች**

የዚህ ጥናት የተለያዩ ክፍሎች ግምገማ አዳዲስ የአገልግሎት ቅርጾች እና አማራጮች እድሎችን ለማየት መሰረት ይጥላሉ። እያንዳንዱ ስራ መጠቃለል ያለበት የሃሳብ እቅድ በማግኘት አላማ ነው። ስራዎቹ መመስረት ያለባቸው በመረጃ ሲሆን ይህም በጥናቱ እስከዚህ ነጥብ ድረስ ነው። ይህ አጠቃላይ አቀራረብ የገበያ ጥናት ትንተና፣ የመሬት አጠቃቀም መጎልበት፣ መሰረተ ልማት፣ ቴክኖሎጂ፣ ስራዎች፣ ገበያ ፍሊጋ እና የህዝብ ተሳትፎን ማጠቃለል አለበት።

1. የአገልግሎት ሃሳቦች እና አማራጮች ሜኑ ማጎልበት
2. እያንዳንዱ ሃሳብ በዝርዝር መቅረብ እና የጥናቱን አላማዎች እንዴት እንደሚመታ መገለጽ አለበት
3. ላሉት ተጓዦች ያለውን ተጽእኖ መግለጽ
4. ለስርኣቱ ብቃት አጠቃላይ መሻሻል መግለጽ
5. የገንዘብ ነክ ተጽእኖውን መግለጽ እናም ለተጨማሪ የድጎማ ምንጮች እድል ካለ ማወቅ
6. ርዕስ 6 አገልግሎት ፍትሓዊነት ትንተናዎች በያንዳንዱ የሚመከር ሃሳብ ላይ መመስረት አለበት።
7. እያንዳንዱ ሃሳብ መጠቃለል ያለበት ለማነጻጸር አላማዎች ነው።
    a. ምርጫ
    b. ዝርዝሮች
    c. ውጤት ወጪ

8. የሚመረጠውን ሃሳብ ምክረ ሃሳብ ያቅርቡ እና ሁሉንም የመመዘኛ ነጥቦች ውጫዊ እና ውስጣዊ ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ጨምሮ በደንብ መግለጽ።

9. የሚመረጠው ሃሳብ መገለጽ ያለበት በክፍል ወይም በጠቅላላ መተግበሩን ነው።
    a. በቁልፍ ክፍሎች ላይ አጽንኦት ማድረግ ይጠየቃል።
    b. ለህዝብ ፎረም ተሳትፎ ያሉትን መረጃዎች ማጎልበት ይጠየቃል።
    c. ለትግበራ የጊዜ ሰሌዳ ማጎልበት ይጠየቃል።
    d. አዲስ የአገልግሎት እቅድ የማጎልበት የገበያ ፍለጋ እቅድ ይጠየቃል።